# በልጆች ላይ የሚደርስ የወሲባዊ ብዝበዛ

ወሲባዊ ብዝበዛ ህገወጥና ድርጊቱም ወንጀል ነው። አንድ ሰው ወሲብን ለንግድ፣ ድርጊቱን በስጦታ ወይም በውለታ መልክ፣ በምግብ፣ በመጠለያ፣ በእፅ፣ በመጠጥ ወይም በገንዘብ ልዋጭነት ከጠየቀ ድርጊቱ ወሲባዊ ብዝበዛ ነው። ልጆች ላይ ወሲባዊ ብዝበዛ ተፈጸመ የምንለው በስልጣን እርከን ላይ ያሉ፣ አዋቂ ግለሰቦች ለምሳሌ እንደ ዘመድ፣ መምህር፣የሀይማኖት አባት፣ወይም ጠበቃ 18 አመት እድሜ ያልሞላቸውን ወጣቶች በማታለል ወሲባዊ ድርጊት ሲፈጽሙ ነው። ወሲባዊ ብዝበዛ ያንድን ወጣት ሰውነት መንካት ወይም መዳሰስ ወይም ወጣቱ/ቷ የሌላን ሰው አካል ወሲባዊ በሆነ ድርጊት እንድትነካካ/እንዲነካካ መጠየቅን ያጠቃልላል።

## ወሲባዊ ብዝበዛ የሚደርስበት ማነው?

ወሲባዊ ብዝበዛ የሚደርስባቸው አብዛኞቹ ሴቶች ሲሆኑ ወንዶችም የዚህ ጥቃት ሰለባ ይሆናሉ። አብዛኛዎቹ በቤተሰብ ግጭት፣በሱስ ወይም በለጋ እድሜአቸው አትኩሮት ያልተሰጣቸውና የሰውነት ወይም የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸው ናቸው። ብዙዎቹ ላጭርም ይሁን ለረጅም ጊዜ ቤት አልባ ሲሆኑ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ጎልማሶች ለወሲባዊ አገልግሎት ይጠቀሙባቸዋል።

## የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ትክክለኛው እድሜ ስንት ነው ?

በካናዳ ግብረስጋን ለመፈጸም የፍቃደኝነት እድሜ 16 ዓመት ነው፤ ወጣቶች እዚህ እድሜ ላይ ከደረሱ እንደአዋቂ ሰለሚገመቱ ወሲብን በተመለከተ ያሻቸውን ውሳኔ ሊወስኑ ይችላሉ። ይም ሲባል ግን ወጣቶቹ ጎልማሳ አለመሆናቸውን መገንዘብ ይገባል። ማኒቶባ ውስጥ ጎልማሳ ተብሎ ለመታሰብ 18 ዓመት መሙላት ግድ ነው። ቢሆንም የ 16 ዓመት ልጆች በፈቃደኝነት ከአዋቂ ሰዎች ጋር ወሲብ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡ ሆኖም ግን ለወሲብ የሚገናኙት ግለሰብ በስልጣን ወይም በታማኝነት ቦታ ላይ ተመድቦ የሚሰራ መሆን **የለበትም** በስልጣን ላይ ያለ ግለሰብ እድሜው ከ 18 ዓመት በታች ከሆነ ወጣት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ከፈጸመ ድርጊቱ ህገወጥ ነው። ጎልማሶችም ለዚህ ህግ የመታዘዝ ሃላፊነት አለባቸው።

## በልጅ ወሲባዊ ብዝበዛ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ምን ሊደርስብዎ ይችላል?

ከ 16 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶችን በማታለል ወሲባዊ ብዝበዛን ከፈጸሙ 10 ዓመት ያህል ሊታሰሩ ይችላሉ። ከካናዳም ሊባረሩ ይችላሉ። በዚህ ባህሪዎም የቤተሰብዎን፣ የማህበረሰቡዎንና የዘርዎን ስም ሊያጎድፉ ይችላሉ። ፖሊስም ስምዎን ከ ቻይልድ አብዩዝ ሬጅስተሪ መዝገብ ውስጥ በማስገባት ድርጊትዎን በይፋ ሌሎች ሰዎች እንዲያዩት ያደርጋል፡ እርስዎም እድሜ ልክዎን በሀፍረት ተሸማቀው እንዲኖሩ ይገደዳሉ፤ ሥራም ሆነ መኖሪያ ለማግኘት ይቸገራሉ።

## በጤናስ ላይ የሚያስከትለው ጦስ ምንድን ነው?

ወሲባዊ ጥቃት ያደረሱባት ወጣት ያባለዘር በሽታ ወይንም የኤች አይ ቪ ቫይረስ ሊኖርባት ይችላል ስለዚህም ያለ ኮንዶም ወሲባዊ ድርጊት ከፈጸሙ በአባለዘር በሽታ ሊያዙ ወይም ያባለዘር በሽታ ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ያባለዘር በሽታ ካለብዎት ደግሞ የ ኤች አይ ቪ ቫይረስ ኤድስን ሊያስከትል ይችላል። ኤድስ እንደሚታወቀው መድሃኒት የሌለው በሽታ ነው፤ በቫይረሱ ለመለከፍዎ ምልክት ስለማይኖረው በ ኤች አይቪ መያዝዎን ላይገነዘቡ ይችላሉ። በቫይረሱ ለመያዝዎ ምልክት ሳይታይብዎ ለወሲብ ወዳጅዎ፣ለባለቤትዎ ወይም ወደፊት ሊወልዷቸው በሚችሏቸው ልጆች ላይ ቫይረሱን ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

## አንድ ሰው በልጅ ላይ ወሲባዊ ብዝበዛ እየፈጸመ እንዳለ ከጠረጠሩ  ምን ማድረግ አለበዎት?

አዋቂዎች ልጆችን ለወሲብ ብዝበዛ እንዳይጋለጡ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው። ለወሲብ ብዝበዛ የተጋለጠ ልጅ ያለ ከመሰለዎና ሁኔታው ያሚያሳስብዎ ከሆነ ስጋትዎን ለፖሊስ፣ ለቻይልድ ና ፋሚሊ ሰርቪስ ወይም ክሊኒክ ውስጥ ለሚገኝ ለተላላፊ አባለዘር በሽታ ክፍል ማሳወቅ አለብዎት። ድርጊቱን ሲጠቁሙ ስምዎን ያለመናገር ይችላሉ። ጥቆማዎም በሚስጥር ይጠበቃል፤ ድርጊቱን እንዴት እንደሚያሳውቁ እርግጠኛ ካልሆኑ  አማካሪን (ካውንስለር) ለእርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።
ከታች የተጠቀሱትን ህገ ወጥ ድርጊቶች ለፖሊስ ማሳወቅ አለብዎት፡-

- አንድ አዋቂ በመንገድ ላይ ከ 18 አመት ያልበለጠን ልጅ ለወሲባዊ ድርጊት ሲጠይቅ ከታዘቡ
- አንድ ሰው ልጆችን ለወሲብ እንደሚያቃጥር ካወቁ
- በኢንተርኔት ላይ ጥቃት የደረሰበት ወይም አፀያፊ ወሲባዊ የልጅ ምስል ካስተዋሉ
- በኢንተርኔት አማካኝነት አንድ ልጅ ለወሲባዊ አገልግሎት ግንኙነት ከፈጠረ
- ለልጆች ወሲባዊ ብዝበዛ ኀብኚዎችን የሚያበረታታ ዌብሳይት ካስተዋሉ
- በአካባቢዎ የልጆችን ወሲባዊ ብዝባዛ የሚያካሂድ ጎረቤት መኖሩን ከተጠራጠሩ
- ልጆች በቤታቸው በትምህርት ቤት ወይም በሌሎች አካባቢዎች የወሲብ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ከተገነዘቡ

ከላይ የተጠቀሱትን ህገወጥ ድርጊቶች ለዊኒፔግ ፖሊስ በስልክ ቁጥር 986-3464 ወይም በኢሜል wps-vice@winnipeg.ca ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚቀጥለውን ዌብ ሳይት ይጎብኙ www.stopsexwithkids.ca